# ትንቢተ ሚልኪያስ (57)

## ጥናት አንድ ሚልኪያስ 1፥1-14

የጥናት ዓላማ፡- በዚህ ዘመን የንጉሥ ካህናት ትብለን የተጠራነው እኛ ሁላችን፤ ልናተኩርበትና ልብ ልንለው የሚገባን ነገር፤ እግዚአብሄርን ለማስደሰት በቤቱ ውስጥ ከምናደርገው የአገልግሎታችን መስዋዕት በተጨማሪ፤ መስዋዕታችን ርኩሰት የሌለበትና ንጹህ መሆኑንም ማረጋገጥ እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በመሰዊያዬ ላይ ከንቱ እሳት እንዳታነዱ፣ ምነው ከእናንተ አንዱ የቤተ መቅደሱን ደጅ በዘጋ ኖሮ! እኔ በእናንተ ደስ አይለኝም፣ ከእጃችሁም ምንም ዓይነት ቁርባን አልቀበልም፣ ይላል እግዚአብሄር ጸባዖት።" ሚል 1፡10

1. ትንቢተ ሚልኪያስ 1፥1-14 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-3ትን ስንመለከት፤ እግዚአብሄር አምላክ ለእስራኤልን ያለውን ስሜት ሲገልጽና እስራኤል ደግሞ ስለሁኔታው የሚያስበውን ሲናገር እናያለን። እግዚአብሄር ለህዝቡ እንዳለው በሚናገረው ስሜትና፤ ህዝቡ ደግሞ እግዚአብሄር ስለ እነርሱ ደግሞ ስለሁኔታው ባላቸው አመለካከት መሃል የምንመለከተው ልዩነት ምንድነው? እስራኤል የእግዚአብሄርን ፍቅር ለመጠራጠር እስኪደርስ የሆነበት ምክንያቱ ምን ይመስልሃል?
2. ቁ4-5 በተለይም ቁ4 ላይ ኤዶምያስ "ብንደመሰስ እንኳን መልሰን እንሰራዋለን ይል ይሆናል" በማለት ይናገራል። በዚህ ቦታ ኤዶምያስ በመባል የተነገረለት በቁ3 ላይ ኤሳው በመባል የተጠራውን የእስራኤልን ወንድም ነው። ቁ4-5ት ላይ ያለውን ሃሳብ ስንመለከት፤ ስለዚህ ኤዶምያስ ወይም ደግሞ ኤሳው ስለተባለው ሰው መንፈሳዊ ሁኔታ ልንረዳ የምንችለው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር አምላክስ፤ ኤዶምያስ ለሚያሳየው ሁኔታ ምላሹ ምን እንደሚሆን ነው የሚነግረን? በእግዚአብሄር ሃሳብና ፈቃድ ላይ ተነስቶ በድል ሊመለስ የሚችል ምንም ዓይነት ፍጥረት ሊኖር እንደማይችል ማወቅ ጥበብ ነው።
3. በቁ6 ላይ እግዚአብሄር ሕዝቡ በራሱ ላይ ያደረገበትን ነገር ከመንገሩ በፊት በሰዎች መሃል የሚታዩትን ሁለት የግንኙነት ዓይነቶች በመጠቀም ነው ንግግሩን የሚጀምረው። እነዚህ እግዚአብሄር ለህዝቡ ሃሳቡን ለማስረዳት ወይም ለማገለጽ የተጠቀመባቸው ሁለቱ የግንኙነት ዓይነቶች ምንና ምንድናቸው? በዚህ ቁጥር ላይ የተጠቀመባቸው ግንኙነቶች ማለትም ልጅና ባሪያ  ማድረግ የሚገባቸው ነገሮች አሉ፤.ታዲያ ይህንን አስመልክቶ በዚህ ዘመንስ የእግዚአብሄር ልጆችና የእግዚአብሄር ባሪያዎች ነን ብለው ከሚናገሩ ሰዎች እግዚአብሄር ምን አይነት ነገሮችን ይጠብቃል?
4. ከቁ6 መጨረሻ አንስቶ እስከ ቁ8 ላይ ያለውን ስናነብ፤ ለሕዝቡ ሁሉ ከመናገር ወጥቶ በተወሰኑ ሰዎች ላይ በማነጣጠር ይህንኑ ከላይ ለሁሉ ይናገርበት በነበረው ሃሳብ ማለትም ስሙን ማቃለልን አስመልክቶ ሲናገር እናገኘዋለን። በዚህ ቦታ እግዚአብሄር ስሙን እንዳቃለሉ ለመናገር ሃሳቡን ያነጣጠረባቸው ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄርን ሥም ማቃለል አድርገው ማየት ያልቻሉት፤ ነገር ግን በእግዚአብሄር ፊት ሲታይ ስሙን ማቃለል እንደሆነ አድርጎ የነገራቸው ነገር ምንድነው? እነዚህ ካህናት በቁ7 ላይ ስንመለከት ቅዱስና ርኩስ የሚለውም ሃሳብም ሁሉ የጠፋባቸው ይመስል "ያረከስንህ እንዴት ነው?" በማለት ለሚጠይቁት ጥያቄ የእግዚአብሄር መልስ ምን ነበረ?
5. "የእግዚአብሄር ገበታ የተናቀ ነው በማለታችሁ ነው።" በማለት በቁ7 ላይ እግዚአብሄር የነገራቸው ነገር፤ እውነት እነዚህ ሰዎች እንዲህ ብለው ተናግረዋል ወይስ እግዚአብሄር ይህንን ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ካህናቱ በእግዚአብሄር ፊት ለመስዋእትነት እያቀረቡ ያሉትን ነገር ለአለቆቻቸው ወይም ለገዥዎቻቸው ማቅረብ ይችሉ እንደሆነ ሲጠይቃቸው፤ ይህንን የገዥ ወይም ለአለቃቸው ጎዶሎ ነገር ማቅረብ አለመቻላቸውን ከራሱ ሁኔታ ጋራ በመናገር ሊያስተምራቸው የፈለገው እውነት ምንድነው ብለህ ትላለህ?
6. ቁ12-14 ላይ በማንበብ እነዚህ ካህናቱ በመሰዊያው ላይ ለእግዚአብሄር እያቀረቧቸው ያሉትን መስዋእቶች በእርሱ ፊት ተቀባይነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጓቸው ምን ተጨማሪ ምክንያቶችን ትመለከታለህ? በተለይም ቁ14ትን ስንመለከት፤ እያደረጉ ያሉት ነገር ከማጣትና ካለማወቅ የተነሳ እንዳልሆነ የምናውቀው እንዴት ነው?
7. በቁ10 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት፤ ለእግዚአብሄር በመሰዊያው ላይ እሳት መንደዱ ብቻውን በቂ ነገር ሆኖ እንዳላገኘው እንረዳለን፤ እግዚአብሄር ጸባዖት ከእሳቱ መንደድ ባሻገር እሳቱን ከሚያነዱት ሰዎች የሚጠብቀው ነገር ምንድነው? አንተስ በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ መሳተፍህን ብቻ እንደ በቂ ነገር አድርገህ ትኩራራበት ይሆን? የንጉሥ ካህናት የሆንን እኛ ሁላችን በአገልግሎታችን መትጋት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ፤ የምንሰዋለት የአግልግሎት መሥዋዕትም ከርኩሰት የጸዳ መሆን እንደሚኖርበት አንዘንጋ።

# ጥናት ሁለት ሚልኪያስ 2፡1-17

የጥናት ዓላማ፦ እኛ የአዲስ ኪዳን አማኞች ሁላችን የንጉሱ የኢየሱስ ካህናት መሆናችንን ጲጥሮስ ያረጋግጥልናል፤ ስለዚህም እንደ እግዚአብሄር መልዕክተኛና አምባሳደር በምድር ላይ እስካለን ድረስ የሰዎችን ለነፍሳቸው ጥያቄ መልስን እንዲያገኙ እግዚአብሄር ያዘጋጀላቸው መንገድ እኛ አማኞች ስለሆንን፤ በትምህርታችን፣ ወይም በአኗኗራችን እንቅፋት የምናኖርባቸው ሰዎች እንዳይኖሩ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ "ካህኑ የሁሉ ገዥ፣ የእግዚአብሄር መልዕክተኛ ስለሆነ ከንፈሮቹ እውቀትን ሊጠብቁ፤ ሰዎችም ከአንደበቱ ትምህርትን ሊፈልጉ ይገባል፤ እናንተ ግን ከመንገዱ ወጥታችኋል፤ በትምህርታችሁም ብዙዎች እንዲሰናከሉ አድርጋችኋል… ይላል እግዚአብሄር ጸባዖት።" ሚክ 2፡7-8

1. ትንቢተ ሚልኪያስ 2፡1-17 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ውስጥ እግዚአብሄር ለካህናቱ እንደገና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ መልዕክቱን ሲናገር እንመለከተዋለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የእግዚአብሄር ካህናት ማስጠንቀቂያውን ለመስማት እንቢ ቢሉ ሊደርሱባቸው የሚችሉት ነገሮች ምን እንደሆኑ ነው የተነገራቸው? በዚሁ ክፍል በቁ2ት ላይና በዘዳ 23፡5 ላይ የሰፈሩትን ሃሳቦች ጎን ለጎን በማነጻጸር ለሚያጠናቸው ሰው፤ በረከትንና እርግማንን አስመልክቶ ሊማር የሚችለው አንድ እውነት ምንድነው ትላለህ?
2. በቁ3-4 ውስጥ ያሉትን ሃሳቦች ስንመለከት፤ እግዚአብሄር አምላክ ካህናቱ በመሰዊያው ላይ ለመስዋእትነት እያቀረቡ ያሉትን መስዋእት ምን በማለት ነው የሚጠራው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር እነዚህ ካህናቶች በነገራቸው መንገድ ካልሄዱና ልባቸውን ስሙን ለማክበር ካላዘነበሉ በቀር ሊያመጣባቸው ያለውን ነገሮች በማስጠንቀቂያ መልክ መናገሩ፤ በአንድ በኩል ቁጣውንና በእነርሱ ደስ አለመደሰቱን የሚያረጋግጥ ነገር ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ማስጠንቀቂያው የሚያከናውነው ነገር ምን እንደሆነ ነው የምናየው?
3. በቁ5 ላይ ከምናነበውና ከምንረዳው ነገር እግዚአብሄር ከሌዊ ጋራ የቃል ኪዳን እንደነበረው ነው። ከእነዚህ ቁጥሮች መረዳት እንደምንችለው በሁለቱ ወገኖች መሃል የተገባውን የቃል ኪዳን ዓይነት እግዚአብሄር ሲገጸው ምን ዓይነት ኪዳን በማለት ነው የሚናገረው? ይህ በእግዚአብሄርና በሌዊ መካከል የነበረው በቁ4ትና በቁ5-6 ላይ የምናነበው ቃል ኪዳን በሁለቱም ወገኖች በኩል በጥሩ ሁኔታ ሃላፊነታቸውን እንደተወጡ የሚጠቁሙን ሃሳቦች የትኞቹ እንደሆኑ ለወገኖች ተናገር።
4. ለቤተ ክርስትያን ብዙ ገንዘብ የሚሰጡ ሃብታም ሰዎችን በዘመናችን ያሉ አንዳንድ አብያተ ክርስትያናት የሚያስተናግዱበትን መንገድ ስንመለከትና በቁ10-12 በተለይም ደግሞ በቁ12 ላይ የተነገረውን ሁኔታ ስታነብ በሁለቱ መሃል ምን ማየት ትችላለህ? የእግዚአብሄር ካህናት በቁ10-12 ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ከማድረግ አልፈው የእግዚአብሄርን መሰዊያ በእንባ እንደሚያጥለቀልቁት ቁ13-14 ውስጥ ይነግረናል። እግዚአብሄር መሰዊያውን በእንባ አጥለቀለቃችሁ ብሎ ሲናገር፤ በተለይ እንደ ባለእንባዎች እንደሆኑ አድርጎ ከፍሉ የሚጠቁመን ማንን እንደሆነ ነው? በእግዚአብሄር ፊት ቃል ኪዳን ለገባንለት ሰው የምናሳየውን ሁኔታ እግዚአብሄር ትኩረት ሰጥቶ እንደሚከታተለው ታውቃለህ ወይ?
5. የእግዚአብሄርን መሰዊያ በእንባ እየሞሉ ነው በመባል የተነገረላቸውን ሰዎች እግዚአብሄር እግዚአብሄር በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይም በቁ14 ላይ የተለያዩ አጠራሮችን  በመጠቀም ሲጠራቸው ይታያል፤ ለእነዚህ ሰዎች የተሰጡትን ቢያንስ አራት መጠሪያዎች ተናገር። በቁ15 ደግሞ በባልና ሚስት አንድነት ላይ ያተኮርን ሃሳብ በማጉላት ሲናገር እናየዋለን። ታዲያ በዚህ ክፍል ከምንመለከተው፤ እግዚአብሄር አንድ የማድረጉ አንደኛው ምክንያት አድርጎ የሚናገረው ነገር ምንድነው?
6. በቁ13-16 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ለትዳር ጓደኞቻችን ሊኖረን የሚገባንን አክብሮትና ጥንቃቄ የተናገረ ሲሆን፤ እግዚአብሄር የሃሳቡ ማጠቃለያ አድርጎ የተጠቀመበትና በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሁለት ጊዜ ሰፍሮ የምናገኘው ሃሳብ ምን እንደሆነ ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ሕዝቡ በትዳር ጓደኞቻቸው ላይ ያደረጉት በነበረው ድርጊት ደስ እንዳልተሰኘ ሲናገር፤ ቁ17 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር ድርጊታቸው ብቻ ሳይሆን ሌላ ያዘነበትን ሁኔታ እንዳለ ይገልጻል፤ ይህ ይሳዘነው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
7. እንደ ቁ7 አነጋገር ሰዎች መመሪያንና ትምህርትን ለማግኘት ወደ ካህኑ እንደሚመጡ ይናገራል። ለምንድነው ካህናት ይህ ሃላፊነት ስለተጣለባቸው ጥንቃቄ ማድረግ የሚኖርባቸው? በምን መንገድ ነው በእኛ ሕይወት ውስጥ ይህንን ግንዛቤ ተግባራዊ ማድረግ የምንችለው? አንተስ ሕይወትህን የእግዚአብሄር መልዕክተኛና አምባሳደር እንደሆነ ሰው ትመራለህ ወይ? አማኞች ሁላችን የአዲስ ኪዳን ካህናት ተብለን የተጠራን፤ እንደ እግዚአብሄር መልዕክተኛና አምባሳደር በምድር ላይ የሰዎችን የነፍስ ጥያቄ የመመለስ እድልና ሃላፊነት የተሰጠን በመሆኑ፤ በቃል ወይም በአኗኗር እንቅፋትን የምናኖርበት ሰው እንዳይኖር መጠንቀቅ ተገቢ ነው።

# ጥናት ሶስት ሚልኪያስ 3፡1-4፡6

የጥናት ዓላማ፡- የስንፍና ንግግር ስንናገር አምላካችንን ከማሳዘን በቀር ሌላ ፋይዳ የሌለው ሲሆን፤ ከወንድሞቻችንና ከእህቶቻችን ጋራ የምናደርገው ንግግርና ጭውውት እግዚአብሄርን መፍራት ያለበት ከሆነ ግን፤ ከዚህኛው ሕይወትም ባሻገር ለሚመጣውም ሕይወት የሚሆነውን መታሰቢያ በእግዚአብሄር ፊት የሚያስቀርልን ነገር እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በዚያን ጊዜ እግዚአብሄርን የሚፈሩ ሰዎች እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ፤ እግዚአብሄር አደመጠ፤ ሰማቸውም፤ እግዚአብሄርን ለሚፈሩና ስሙን ለሚያከብሩ በእርሱ ፊት የመታሰቢያ መጽሐፍ ተጻፈ።" ሚል 3፡16

1. ትንቢተ ሚልኪያስ 3፡1-4፡6 በአንድነት ይነበብ። ሚል 3፡1-5ትን በምናነብበት ጊዜ ሁለት ዓይነት መልዕክተኞች እንዳሉ እንረዳለን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ የምናያቸው ሁለቱ መልዕክተኞች ማንና ማን እንደሆኑ ነው የምታምነው? ይህ የእግዚአብሄር መልዕክተኛ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመግለጽ በዚህ ክፍል ውስጥ ነብዩ የተጠቀመባቸው ሁለት ዓይነት ነገሮች እንዳሉ እናነባለን፤ እነዚህ ሁለቱ የኢየሱስን ማንነት ለማንጸባረቅ የተጠቀመባቸው ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነዚህን ሁለት ነገሮች የሚመሳሰሉባቸው ባህርይ ምን እንደሆነ በተለይም ከካህናቱ ጋራ አዛምደህ ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ።
2. ቁ6-9ን ስናነብ የእስራኤል ልጆች እግዚአብሄርን በመስረቃቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ነገር በአንድ ቃል ብቻ በማጠቃለል ተናገር ብትባል ምን ትላለህ? በቁ6 ላይ የእግዚአብሄርን ያለመለወጥ ባህርይ ከያዕቆብ አለመጥፋት ጋራ አያይዞ ሲናገር እንመለከተዋለን። በአንተ አመለካከት፤ የእግዚአብሄር አምላክ አለመለወጥና የያዕቆብ አለመጥፋት የሚገናኙበት ወይም ደግሞ ይህ ሃሳብ ወሳኝነት የሚኖረው በምን መንገድ እንደሆነ ተናገር። የእግዚአብሄር አለመለወጥ ለአንተስ ምን ያህል ወሳኝነቱ ይታይሃል?
3. ቁ10-11 ላይ ስናነብ ሕዝቡ የእግዚአብሄርን ማስጠንቀቂያና ትዕዛዝ በመከተል የተባለውን ነገር ማድረግ ቢጀምር፤ እግዚአብሄር አምላክ ሊያደርግ ያለውን ነገር ይነግራቸዋል። በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ እንደሚያደርግላቸው የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ በሁለት ዋና ዋና ሃሳቦች በማጠቃለል ለመናገር ሞክር።
4. በሚል 3፡14-15 ላይ በተለይም ደግሞ ቁ14ትን ስናይ እነዚህ እግዚአብሄርን እናገለግላለን የሚሉት ካህናቱ ሁለት ከንቱ አድርገው የሚመለከቷቸውና የሚነጋገሩባቸው ነገሮች እንዳሉ እንመለከታለን። እነዚህ ሁለት ጥቅም የላቸውም ብለው የሚናገሯቸው ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነርሱ እንዲኖሩ ከሚጠበቅባቸው የሕይወት ዓይነት ይልቅ፤ እነዚህ ካህናት እያስቀናቸውና ልባቸውን እየሳበ ያለ ሌላ የሕይወት ዓይነት እንዳለ ነው የሚነግሩን፤ ይህ ያጓጓቸው የህይወት ዓይነት ምን እንደሆነ ተናገር።
5. ከላይ በተመለከትናቸው ቁጥሮች ላይ ካህናቱ ያላቸው አመለካከት የተሳሳተ አስተሳሰብ እንደሆን በቁ18 ላይ እግዚአብሄር ከሚናገረው አነጋገር መረዳት እንችላለን። እነዚህ ካህናት ላቀረቧቸው ጥያቄዎችና ላሳዩት የጥርጥር መንፈስ ቁ18 ላይ እግዚአብሄር የሚናገረው ሃሳብ በምን መንገድ መልስ ሊሆናቸው ይችላል ብለህ ታምናለህ?
6. በቁ15 ላይ ካህናቱ በቅናት ስለተናገሩላቸው ትዕቢተኞችና ክፉ አድራጊዎች በሚልኪያስ 4፡1-3 ውስጥ እግዚአብሄር ሊስልላቸው የሚሞክረው ስዕል ምን ይመስላል? በዚህ ሥፍራ የተመለከትነውን የክፉዎች ጊዜያዊ የሕይወት ክንውንና እንዲሁም እግዚአብሄር እያየላቸው ያለውን ፍጻሜ በመዝ 37፡34-36 ላይ ዳዊት ከሚናገረው እውነት ጋራ በማነጻጸር ለመናገር ሞክር።
7. በሚል 4፡4-6 ውስጥ ያለውን ሃሳብ ስናነብ፤ በተለይም ቁ5 እና ቁ6 ላይ የተነገሩት ሃሳቦች ተፈጻሚነታቸው ገና ወደፊት የሚሆን ነገር እንደሆነ እናያለን። ታዲያ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እየተነገሩ ያሉት ሃሳቦች በማን ላይ ያነጣጠሩ ወይም ደግሞ ስለ ማን እየተናገሩ ነው ብለህ ታምናለህ? እግዚአብሄር ለህዝቡ በተለያዩ ብዙ ነብያት ከተናገረ በኋላ ይህ የሚልኪያስ ትንቢት አራት መቶ ዓመታት የዝምታ ጊዜ ውስጥ ከመገባቱ አስቀድሞ ለመጨረሻ ጊዜ የተናገረ ነብይ እንደሆነ እናውቃለን። ከሚልኪያስ በኋላ ለሕዝብ በግልጽ ሲናገር የምናገኘው ነብይ ማን ነው?
8. መለስ ብለን በሚል 3፡16 ላይ የተነገረውን ሃሳብ ስንመለከት፤ በዚያው ምዕራፍ ቁ14-15 ላይ በጊዜው የእግዚአብሄር አገልጋዮች የነበሩት ካህናት እየተናገሩ ካሉት ሃሳብ ለየት ያለ ነገርን እናነባለን። በዚህ ሥፍራ ላይ እየተነጋገሩ ያሉትን ሰዎች እነማን በማለት ነው የሚጠራቸው? የእነዚህ ሰዎች ንግግር ከካህናቱ ንግግር ምን የተለየ ውጤት እንዳስገኘ ታያለህ? የአንተስ አንደበት ካህናቱ እንደተናገሩት የስንፍና ነገርን ወይስ እግዚአብሄርን መፍራት ያለበት ነገር ይናገራል? እግዚአብሄርን መፍራት የሞላበት ንግግር ከዚህኛው ሕይወትም ባሻገር ለሚመጣውም ሕይወት የሚሆነውን መታሰቢያ በእግዚአብሄር ፊት የሚያስቀርልን እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል።